መመሪያ ቁጥር 04/2015

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ለመመልመልና የመሥሪያ ቦታ/መሬት/ መጠን ወስኖ ለመስጠት ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ

በክልላችን የአምራች ኢንዱስትሪዉን ዘርፍ በተገቢዉ መንገድ በመደገፍና በማጠናከር የክልሉን ኢኮኖሚ ከፍ እንዲል ለማድረግ፤

ተመጋጋቢ የሆኑ አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም፣ በማስፋፋትና በማሳደግ የክልሉን ብሎም የአገሪቱን ኢኮኖሚ ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር በየደረጃው የሚገኘውን የሕብረተ-ሰብ ክፍል ተጠቃሚ ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፤

በኢኮኖሚው ዘርፍ የላቀ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን በልዩ ሁኔታ ለመደገፍ፣ ለኢንዱስትሪ ልማት አገልግሎት የሚውል የተፈጥሮ ሀብትና መሰረተ ልማት አቅርቦትን /መንገድ፣ ውኃ፣ መብራት/ ለተገቢው ዓላማ በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ፤

ወደ ተቀናጁ ኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ ሁሉ-ገብ ኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ ከሁለገብ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውጭ የሚገቡ የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ለመመልመልና የቦታ መጠንን ለመወሰን ቢሮው የሚፈፅማቸውን ተግባራት ለይቶ ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤
ቀደም ሲል በቢሮው የተዘጋጀው መመሪያ ቁጥር 01/2013 በትግበራ ወቅት በተነሱት ጥያቄዎች መሠረት መብራራት፣ መካተትና መሻሻል ያለባቸው አንቀጾች በመኖራቸው፤
በዚህም መሰረት ወደ ተቀናጀ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ሁለገብ ኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ ከሁለገብ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውጭ የሚገቡ የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ለመመልመልና የቦታ መጠን ለመወሰን ቢሮው የሚፈፅሟቸውን ተግባራት ለይቶ ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ የአብክመ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለዉ የአስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 280/2014 አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1/ሰ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አሻሽሎ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ለመመልመልና የመሥሪያ ቦታ/መሬት/ መጠንን ወስኖ ለመስጠት ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 04/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ

(1) **"አዋጅ"** ማለት በፌደራሉ መንግሥት የወጣው የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 1180/2012 ነው፤

(2) **"ቢሮ"** ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ሲሆን፤ በስሩ የተደራጁ መዋቅሮቹንም ይጨምራል፤

(3) **"ኮርፖሬሽን"** ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽንን እና በስሩ የተዋቀሩ ተቋማትን ያመለክታል፤

(4) **"የኢንዱስትሪ ክላስተር ማዕከል"** ማለት ከሁሉ-ገብ ኢንዱስትሪ ፓርክና ከተቀናጀ ኢንዱስትሪ ፓርክ ትስስር ሊፈጥር የሚችል የኢንዱስትሪ ዕድገት ዓላማዎችን እንደ መንገድ፣ ውሃ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎትና የመሳሰሉት አስፈላጊ የመሠረተ-ልማት አውታሮች ተሟልተውለት ጥሬ ዕቃዎችን ተቀብለው በከፊል ሊያመርቱ የሚችሉ አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን ለማልማት የሚቋቋምና ወሰን ያለው ቦታ ሁኖ ከዚህ በፊት ለአነስተኛ ተቋማት መሥሪያና መሸጫ የተገነቡ ህንጻዎችና ሸዶችን ይጨምራል፤

(5) **"የኋልዮሽና የፊትዮሽ የኢኮኖሚ ትስስር"** ማለት የግብአት አቅራቢነትና የምርት ተቀባይነት ትስስር ማለትም በአካባቢው የሚመረተውን የግብርናና የኢንዱስትሪ ውጤት በግብአትነት የሚጠቀም፣ የአመረተውን ምርት ለሌሎች ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት ሊያቀርብ የሚችል ነው፤

(6) **"ያለቀለት የኢንዱስትሪ ምርት"** ማለት ማሽንን ወይም መሣሪያን ተጠቅሞ ጥሬ ዕቃን ወይም በከፊል የተቀነባበረ የኢንዱስትሪ ውጤትን በማቀነባበር የመጠን፣ የቅርፅ ወይም የይዘት ለውጥ በማድረግና በማሻሻል ለውጭ ገበያ ወይም ለተጠቃሚ የሚቀርብ ምርት ነው፤

(7) **"በከፊል ያለቀለት ምርት"** ማለት ማሽንን ወይም መሣሪያን ተጠቅሞ ጥሬ ዕቃን በመጠቀም የመጠን፣ የቅርፅ ወይም የይዘት ለውጥ በማድረግና በማሻሻል ለሌሎች ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት የሚያገለግል ምርት ነው፤

(8) **"ሁለ-ገብ ኢንዱስትሪ ፓርክ"** ማለት ከተቀናጀ የኢንዱስትሪ ፓርክ ውጭ ያለ ሆኖ ሁሉም አይነት ኢንዱስትሪዎች የሚቋቋሙበት፣ በየዘርፎቻቸው የሚደራጁበትና አስፈላጊ መሠረተ-ልማት የተሟላለት የኢንዱስትሪ ክላስተር ወይም የኢንዱስትሪ ዞንን እና የኢንዱስትሪ ሸዶችን የያዘ ፓርክ ነው፤

(9) **"የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ"** ማለት በክልል ደረጃ በልዩ ሁኔታ የግብርና ምርቶችን የሚጠቀም የአግሮ-ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ፓርክ ነው፤

(10) **"አነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪ"** ማለት የኢንዱስትሪዉን ባለቤት፣ የቤተ-ሰቡን አባላትና ተቀጣሪ ሠራተኞችን ጨምሮ ከ11 እስከ 50 ሰዎችን በቋሚነት የሚያሰማራና የጠቅላላ የሃብት መጠኑ ከብር 600,001 እስከ 10.000,000 ብር (ከስድስት መቶ ሺህ አንድ ብር እስከ አስር ሚሊዮን ብር) የሆነ ኢንዱስትሪ ነዉ፤

(11) **"መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪ"** ማለት የኢንዱስትሪዉን ባለቤት፣ የቤተ-ሰቡን አባላትና ተቀጣሪ ሠራተኞችን ጨምሮ ከ51 እስከ 100 ሰዎችን በቋሚነት የሚያሠራና የጠቅላላ የሃብት መጠኑ ከብር ከ10.000,001 ብር እስከ 90,000,000 ብር (ከአስር ሚሊዮን አንድ ብር እስከ 90 ሚሊዮን ብር) የሆነ አምራች ኢንዱስትሪ ነዉ፤

(12) **"ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪ"** ማለት የኢንዱስትሪዉን ባለቤት፣ የቤተሰቡን አባላትና ተቀጣሪ ሠራተኞችን ጨምሮ ከ100 በላይ ሰዎችን በቋሚነት የሚያሠራና የጠቅላላ የሃብት መጠኑ ከብር ከ90,000,000 ብር (ዘጠና ሚሊዮን ብር) በላይ የሆነ አምራች ኢንዱስትሪ ነዉ፤

(13) **"የወጭ ምርት"** ማለት በአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ተመርቶ ለውጪ ገበያ የሚቀርብ ሸቀጥ/ምርት ነው፤

(14) **"ፕላንት ሌይ አውት"** ማለት በአንድ ፋብሪካ ውስጥ ያሉትን የማምረቻ ክፍሎች፣ የማምረቻ ማሽኖች፣ ቁሳቁሶች፣ አገልግሎት የሚሰጡ ክፍሎችን ማለትም የጥሬ ዕቃ ማስቀመጫ፣ የምርት ማስቀመጫ፣ የጥገና ክፍል፣ መጫኛና ማውረጃ ቦታን፣ የአስተዳደር ቢሮ፣ የስልጠና ክፍል፣ የአትክልት ቦታን፣ መፀዳጃ ቤትን፣ የማረፊያ ክፍልን፣ የህክምና ክፍልን፣ ሎከርን፣ የመዝናኛ ክፍልን፣ የጥበቃ ክፍልን፣ የመኪና ማቆሚያ የመሳሰሉትን በሥርዓት በማደራጀት ለእያንዳንዱ ክፍልና ማሽነሪ የሚያስፈልገውን የቦታ ስፋት በማስላት

ፋብሪካው በምርት ጥራትም ሆነ ብዛት ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችል የቦታ አደረጃጀት ነው፤

(15) **"ማሽን ሌይ አውት"** ማለት ለምርት ማምረቻ የሚያስፈልጉ ማሽኖች የሚያርፉበት፣ ለዕለታዊ ፍጆታ የሚሆኑ ጥሬ ዕቃዎች የሚቀመጡበትና ለሠራተኛው እንቅስቃሴ የሚያስፈልግ የቦታ ወይም የመሬት መጠን በካሬ ሜትር ስፋት ነው፤

(16) **"አምራች ኢንዱስትሪ"** ማለት ማንኛውም የንግድ ተግባር ሆኖ በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ ወይም ለማምረት የሚያገለግሉ ግብዓቶች፣ ማሽን፣ ቴክኖሎጂና የሰው ኃይልን በመጠቀም ምርት የማምረት እና አገልግሎት መስጠትን ይጨምራል፤

(17) **"የቴክኖሎጂ ሽግግር"** ማለት ዕቃዎችን ከመሸጥ ወይም ከማከራየት ውጭ ሆኖ ምርትን ለማምረት ወይም የአመራረት ሂደትን ተግባራዊ ለማድረግ ወይም ለማሻሻል ወይም አገልግሎት ለመስጠት የሚረዳ ሥርዓት ያለው ዕውቀት ማስተላለፍ ሲሆን የሥራ አመራር እና የቴክኒክ ዕውቀት፣ የግብይት እና ቴክኖሎጂንም የሚጨምር ሲሆን፤ ዕቃዎችን ብቻ ለመሸጥ ወይም ለማከራየት የሚደረግን ግንኙነት አይሸፍንም፤

(18) **"ገምጋሚ ኮሚቴ"** ማለት መካከለኛ እና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የመሥሪያ ቦታ እንዲሰጣቸው ያቀረቡትን ጥያቄ መነሻ በማድረግ የመሥሪያ ቦታ አሰጣጥንና መጠንን ገምግሞ ለቢሮው የውሳኔ ሀሳብ ለማቅረብ የተቋቋመ ኮሚቴ ነው፤

(19) **"ባንክ ትራንዛክሽን"** ማለት በፋይናንስ ተቋም ውስጥ በተወሰነ ጊዜ የሚታየውን የገንዘብ ገቢና ወጭ በማስላት የባለሀብቱን አቅም ለማወቅና ጤናማ የሆነ የገንዘብ እንቅስቃሴ መኖሩን ለማረጋገጥ የሚጠቅም ሰነድ ነው፤

(20) **"ኢንድ ባላንስ"** ማለት በፋይናንስ ተቋም /ባንክ/ ዉሥጥ ከጠቅላላ ገቢ ላይ ጠቅላላ ወጭ ተቀንሶ የሚታይ ሂሳብ ስሌት ነዉ፤

(21) **"ዝግ አካዉንት"** ማለት በፋይናንስ ተቋም /ባንክ/ ዉስጥ ላልተወሰነ ጊዜ እንዳይንቀሳቀስ በቢሮዉ ታግዶ የሚቆይ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ነዉ፤

(22) **"ባለሀብት"** ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ ካፒታል ሥራ ላይ ያዋለ የአገር ውስጥ ወይም የውጭ ባለሀብት ነው፤

(23) **"የአገር ውስጥ ባለሀብት"** ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ ካፒታል ሥራ ላይ ያዋለ፡-

ሀ) ኢትዮጵያዊ ዜጋ፣

ለ) ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያዊ ዜጋ የተያዘ ኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋመ ድርጅት፤

ሐ) መንግሥት፣

መ) የመንግሥት የልማት ድርጅት፣

ሠ) አግባብነት ባለው ሕግ የተቋቋመ የሕብረት ሥራ ማኅበር፣

ረ) አግባብነት ባለው ሕግ ወይም ኢትዮጵያ ባጸደቀችው ዓለም-አቀፍ ስምምነት መሠረት እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት የተቆጠረ የውጭ አገር ዜጋ ወይም ድርጅት፤

ሰ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 23 ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ ረ) በተመለከቱት በማናቸውም መካከል በጋራ ኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋመ ድርጅት፣

ሸ) የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 1180/2012 ሲወጣ የአገር ውስጥ ባለሀብት እና አሁንም ኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ ያለ የውጭ አገር ዜጋ ወይም ድርጅት፣ ወይም

ቀ) ከዚህ በላይ በፊደል ተራ (ሸ) መሠረት የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጠው የአገር ውስጥ ባለሃብት ኢንቨስትመንትን በተመለከተ ብቻ ሆኖ በዚሁ ንዑስ አንቀጽ የተመለከተውን የውጭ አገር ዜጋ ተወላጅ ነው፤

(24) **"የውጭ ባለሀብት"** ማለት የውጭ ካፒታል ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት ሥራ ላይ ያዋለ፦

ሀ) የውጭ አገር ዜጋ፣

ለ) የውጭ አገር ዜጋ በባለቤትነት የተሳተፈበት ድርጅት፣

ሐ) በማንኛውም ባለሀብት ውጭ አገር የተቋቋመ ድርጅት፣

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (24) ፊደል ተራ (ሀ) ፣ (ለ) ወይም (ሐ) በተመለከቱት ማናቸውም ባለሀብቶች መካከል በጋራ የተቋቋመ ድርጅት ወይም፤

ሠ) እንደ ውጭ ባለሀብት መቆጠር የፈለገ መደበኛ ነዋሪነቱ ውጭ አገር የሆነ ኢትዮጵያዊ ነው፤

(25) **"ግንባታ መጀመር"** ማለት በቦታው ላይ ለመሥራት ከተፈቀደው ግንባታ ወይም ህንጻ ቢያንስ የመሠረት ሥራ መሥራትና የኮለን ግንባታ ለማከናወን የሚያስችሉ የኮለን ብረቶች የማቆም ሥራ ማጠናቀቅ ነው፤

(26) **"ግንባታ ማጠናቀቅ"** ማለት በሊዝ የተፈቀደ ቦታ ላይ እንዲገነባ የተፈቀደን ግንባታ በተሰጠው የግንባታ ፈቃድ መሠረት ሙሉ በሙሉ መሥራትና ዋና ዋና አገልግሎቶች ተሟልተውለት ለአገልግሎት ዝግጁ ማድረግ ነው፤

(27) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

(28) በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀ ማናቸውም ድንጋጌ የሴትንም ጾታ ይጨምራል።

3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በገጠርም ሆነ በከተማ ወደ ሁለ-ገብ ኢንዱስትሪ መንደር/ፓርክ፣ ከሁለ-ገብ ኢንዱስትሪ መንደር/ፓርክ ውጭ፣ እንዲሁም የተቀናጀ ኢንዱስትሪ ፓርክ በለማባቸው እና ወደ ፊትም በሚለማባቸው ከተሞች/ወረዳዎች ወይም እንደ አስፈላጊነቱ በክልሉ በልዩ ሁኔታ በሚመረጡ ቦታዎችና አካባቢዎች በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለመሰማራት ፍላጎት ባላቸው መካከለኛ እና ከፍተኛ ፕሮጀክቶች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል።

ክፍል ሁለት

የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ማሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች፣ መመልመያ መስፈርት፣ የመሥሪያ ቦታ /መሬት/ መጠን አወሳሰንና አሰጣጥ

4. የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ማሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች

(1) ያለቀለትና በከፊል ያለቀለት የኢንዱስትሪ ምርት የሚያመርቱ መካከለኛ እና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ከሆኑ፤

(2) ለሚወስዱት የመሥሪያ ቦታ/መሬት/ በሊዝ አዋጁ የተቀመጠውን መነሻ የሊዝ ኪራይ መክፈል የሚችሉ ከሆኑ፤

(3) በባህር ዳር፣ ጎንደር፣ ኮምቦልቻ፣ ደብረ-ብርሃን፣ ደብረ-ማርቆስ፣ ቡሬ እና ቁለፋ፣ ከተሞች የሚገቡ ባለሀብቶች ፕሮጀክት አቅርበው በእጩነት ሲመዘገቡ የአገር ውስጥ ባለሀብት ከሆነ/ች በቅድሚያ ቢያንስ የ6 ወር የባንክ ትራንዛክሽን የጠቅላላ ኢንቨስትመንት ካፒታሉን 10 በመቶ ከወጪ ቀሪ ኢንድ ባላንስ ያላቸው መሆኑን ከባንክ/ማይክሮ ፋይናንስ የሚያቀርቡ ሲሆን በዉጭ አገር የሚኖር ትዉልደ-ኢትዮጵያዊ ባለሃብት ከሆነ/ች ደግሞ በአገር ዉስጥ ባንኮች ወይም በዉጭ አገር ባንኮች ወይም በሁለቱም ባንኮች የተገለጸዉን የባንክ ትራንዛክሽን ማቅረብ የሚችሉ ከሆነ፤

(4) ደብረ-ታቦር፣ እንጅባራ፣ ደሴ፣ ከሚሴ፣ ገንዳ ዉኃ፣ ወልድያ እና ፍኖተ-ሠላም ከተሞች የሚገቡ ባለሃብቶች ፕሮጀክት አቅርበዉ በእጩነት ሲመዘገቡ የአገር ውስጥ ባለሀብት ከሆነ/ች በቅድሚያ ቢያንስ የ6 ወር የባንክ ትራንዛክሽን የጠቅላላ ኢንቨስትመንት ካፒታሉን 5 በመቶ ከወጭ ቀሪ ኢንድ ባላንስ ያላቸው መሆኑን ከባንክ/ማይክሮ ፋይናንስ የሚያቀርቡ ሲሆን በዉጭ ሃገር የሚኖሩ ትዉልደ ኢትዮጵያዊ ባለሃብት ከሆነ/ች ደግሞ በአገር ዉስጥ ባንኮች ወይም በዉጭ አገር ባንኮች ወይም በሁለቱም ባንኮች የተገለጸዉን የባንክ ትራንዛክሽን ማቅረብ የሚችሉ ከሆነ፤

(5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) ከተገለጹት ከተሞች ውጭ የሚገቡ የአገር ውስጥ ባለሀብት ከሆነ/ች በቅድሚያ ቢያንስ የ3 ወር የባንክ ትራንዛክሽን የጠቅላላ ኢንቨስትመንት

ካፒታሉን 3 በመቶ ከወጭ ቀሪ ኢንድ ባላንስ ከባንክ/ማይክሮ ፋይናንስ የሚያቀርቡ ሲሆን በዉጭ አገር የሚኖር ትዉልደ-ኢትዮጵያዊ ባለሃብት ከሆነ/ች ደግሞ በሃገር ዉስጥ ባንኮች ወይም በዉጭ ሃገር ባንኮች ወይም በሁለቱም ባንኮች የተገለጸዉን የባንክ ትራንዛክሽን ማቅረብ የሚችሉ ከሆነ፤

(6) በዚህ አንቀጽ ከንኡስ አንቀጽ (3) እስከ (5) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በቢሮ ደረጃ የሚገመገሙ ፕሮጀክቶች በቅድሚያ የ6 ተከታታይ ወራት የባንክ ትራንዛክሽን የጠቅላላ ኢንቨስትመንት ካፒታሉን 15 በመቶ ከወጭ ቀሪ ኢንድ ባላንስ ያላቸው መሆኑን ከባንክ/ማይክሮ ፋይናንስ የሚያቀርቡ መሆን አለባቸው፡፡

(7) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (3) እስከ (6) በተጠቀሱት እና በሌሎች ከተሞች/ወረዳዎች/ ለማልማት የመጣ የውጭ አገር ባለሀብት ከሆነ/ች በፌደራል ኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 1180/2012 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በብሔራዊ ባንክ በኩል የባንክ ሂሳብ ተከፍቶ 200,000.00 /ሁለት መቶ ሽህ/ የአሜሪካን ዶላር ያስቀመጠ መሆኑን ከብሄራዊ ባንክ /ከዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር/ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል ከሆነ፤

(8) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (3) እስከ (6) የተገለጸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የዉጭ አገር ባለሃብት ከአገር ዉስጥ ባለሃብት ጋር በቅንጅት ለማልማት የሚመጣ ከሆነ በፌደራል ኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 1180/2012 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት በብሔራዊ ባንክ በኩል የባንክ ሂሳብ ተከፍቶለት 150,000.00 /አንድ መቶ ሃምሳ ሽህ /የአሜሪካን ዶላር ያስቀመጠ መሆኑን ከብሔራዊ ባንክ /ከዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር/ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል ከሆነ፤

(9) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (3) እስከ (6) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በፒ.ኤል.ሲ፤ በሽርክና እና በአክሲዮን ለተመዘገበ ፕሮጀክት የሚቀርበው የአቅም ማሳያ የባንክ ትራንዛክሽን በፒ.ኤል.ሲዉ፤ በሽርክናዉ እና በአክሲዮኑ ስም ብቻ የተመዘገበ ካፒታል ከሆነ፤

(10) ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (9) የተገለጸዉ ቢኖርም በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) እና (4) ከተጠቀሱት ከተሞች ዉጭ ባሉ ከተሞች በፒ.ኤል.ሲ ለተመዘገበ ፕሮጀክት የሚቀርበው የአቅም ማሳያ የባንክ ትራንዛክሽን በፒ.ኤል.ሲዉ ወይም በአባላቱ ስም የተመዘገበ ካፒታል ከሆነ፤

(11) በፒ.ኤል.ሲ፤ በሽርክና እና አክሲዮን የሚቀርብ ፕሮጀክት መመሥረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ ከፕሮጀክቱ ጋር አብሮ ማቅረብ የሚችል ከሆነ፤

(12) ከዚህ በፊት በአገራችንም ሆነ በክልላችን ፋብሪካ ተክለው በማምረት ላይ ያሉ የአገር ውስጥ ወይም የዉጭ አገር ባለሀብቶች ከሆኑ ልምዳቸውን ለመጠቀም ሲባል በተመሳሳይ ወይም በተለየ የሥራ መስክ አዲስ ፕሮጀክት ሲያቀርቡ የነባሩ ፋብሪካ አፈጻጸም ሲገመገም፡-

ሀ) በፕሮጀክቱ ዕቅድ ላይ በተቀመጠው የማምረት አቅም 50% እና በላይ እያመረቱ ከሆኑ፣

ለ) በፕሮጀክቱ ዕቅድ ላይ በተቀመጠው የሥራ ዕድል ፈጠራ 70% እና በላይ ቋሚ የሥራ እድል የፈጠሩ ከሆኑ፣

ሐ) በፕሮጀክቱ እቅድ መሠረት ምርታቸውን ወደ ውጭ መላክ የጀመሩ ከሆነ፣

መ) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (9) እስከ (11) ከተገለጹት ቢያንስ ሁለቱን የሚያሟሉ ከሆነ፣ ለአንድ ፕሮጀክት ብቻ ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታ የሚስተናገዱ ሲሆን ይህን ካላሟሉ ግን በዚህ አንቀጽ ከንኡስ አንቀጽ (3) እስከ (6) መሰረት የሚስተናገዱ ይሆናል፤

(13) ለግምገማ የሚቀርቡት ፕሮጀክቶች በአራቱ ንዑስ ዘርፎች ብቻ የሚሰማሩ ሲሆን እነሱም፤-

ሀ) በጨርቃጨርቅ ቆዳና አልባሳት ንዑስ ዘርፎች፣

ለ) በአግሮ-ፕሮሰሲንግ፣ ምግብና ፋማሲዮቲካል ንዑስ ዘርፎች፣

ሐ) በእንጨትና ብረታብረት ንዑስ ዘርፎች እና

መ) በኮንስትራክሽን ግብዓትና ኬሚካል ንዑስ ዘርፎች፤

5. መመልመያ መስፈርት

ከላይ በአንቀፅ 4 ንዑስ አንቀጽ (13) የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው በማምረቻና ማቀነባበሪያ ዘርፍ ውስጥ ለመሰማራት የሚቀርብ ፕሮጀክት ከየንዑስ ዘርፉ አኳያ የነጥብ ክብደቱ እየታየ የሚመዘን ሲሆን የማወዳደሪያ መስፈርቱም፡-

(1) የወጭ ምርት መጠን 10 በመቶ፤

(2) ተኪ ምርት የሚያመርቱ 10 በመቶ፤

(3) የሥራ ዕድል ፈጠራ 20 በመቶ፤

(4) የኢንቨስትመንት ካፒታል መጠን 25 በመቶ፤

(5) የአገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ አጠቃቀም 10 በመቶ፤

(6) የቴክኖሎጅ ዕድገት አስተዋጽኦ 10 በመቶ፤

(7) የአምራች ኢንዱስትሪዎች ትስስር ያለዉ 15 በመቶ ሲሆን፤

(1) የውጭ ምርት መጠን 10 በመቶ የሚይዝ ሆኖ

ሀ) አግሮ-ፕሮሰሲንግ፣ ምግብና ፋርማሲዮቲካል ንዑስ ፕሮጀክቶች የወጭ ምርት መጠን፦

1. ከአጠቃላይ ምርቱ ውስጥ 50 በመቶ እና በላይ ወደ ውጭ ገበያ የሚልክ ፕሮጀክት ወይም የተገለጸውን መጠን ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ፋብሪካዎች በግብዓትነት የሚያቀርብ ፕሮጀክት 10 ነጥብ ይሰጣል፣
2. ከአጠቃላይ ምርታቸው ውስጥ ከ50 በመቶ በታች የሚልኩ ፕሮጀክቶች ወይም ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ፋብሪካዎች በግብዓትነት የሚያቀርብ ፕሮጀክት የከፍተኛውን ነጥብ መነሻ በማድረግ በስሌት የሚሰራ ሲሆን፤

ለምሳሌ አንድ 30% ወደ ውጭ ገበያ የሚልክ ፕሮጀክት ወይም የተገለጸውን መጠን ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ፋብሪካዎች በግብዓትነት የሚያቀርብ ፕሮጀክት ቢሆን፤ የውጤት አሠራሩ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

(30*10) /50 = 6 ነጥብ ያገኛል ማለት ነው፤

ለ) ጨርቃጨርቅ፣ አልባሳት፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች ንዑስ ዘርፍ ፕሮጀክቶች፡

1. ከአጠቃላይ ምርቱ ውስጥ 60 በመቶ እና በላይ ወደ ውጭ ገበያ እንደሚልክ የገለፀ ፕሮጀክት ወይም የተገለጸውን መጠን ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ፋብሪካዎች በግብዓትነት የሚያቀርብ ፕሮጀክት 10 ነጥብ ይሰጣል፣
2. ከአጠቃላይ ምርቱ ውስጥ ከ60 በመቶ በታች የሚልክ ፕሮጀክት ወይም ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ፋብሪካዎች በግብዓትነት የሚያቀርብ ፕሮጀክት የከፍተኛውን ነጥብ መነሻ በማድረግ በስሌት የሚሠራ ይሆናል፡

ሐ) እንጨት እና ብረታብረት ንዑስ ዘርፍ ፕሮጀክቶች፡

1. ከአጠቃላይ ምርቱ ውስጥ 40 በመቶ እና በላይ ወደ ውጭ ገበያ እንደሚልክ የገለፀ ፕሮጀክት ወይም የተገለጸውን መጠን ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ፋብሪካዎች በግብዓትነት የሚያቀርብ ፕሮጀክት 10 ነጥብ ይሰጣል፣
2. ከአጠቃላይ ምርቱ ውስጥ ከ40 በመቶ በታች የሚልክ ፕሮጀክት ወይም ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ፋብሪካዎች በግብዓትነት የሚያቀርብ ፕሮጀክት የከፍተኛውን ነጥብ መነሻ በማድረግ በስሌት የሚሠራ ይሆናል፣

መ) ኮንስትራክሽን ግብዓት እና ኬሚካል ማምረቻ ንዑስ ዘርፍ ፕሮጀክቶች፡

1. ከአጠቃላይ ምርቱ ውስጥ 40 በመቶ እና በላይ ለውጭ ገበያ እንደሚልክ የገለፀ ፕሮጀክት ወይም የተገለጸውን መጠን ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ፋብሪካዎች በግብዓትነት የሚያቀርብ ፕሮጀክት 10 ነጥብ ይሰጣል፣
2. ከአጠቃላይ ምርቱ ውስጥ ከ40 በመቶ በታች የሚልክ ፕሮጀክት ወይም ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ፋብሪካዎች በግብዓትነት የሚያቀርብ ፕሮጀክት የከፍተኛውን ነጥብ መነሻ በማድረግ በስሌት የሚሠራ ይሆናል፣

(2) ተኪ ምርት የሚያመርቱ 10 በመቶ የሚይዝ ሲሆን፡-

ሀ) ተኪ ምርት ማምረት የሚችል አምራች ኢንዱስትሪ እንደየንዑስ ዘርፉ ክብደት የሚያገኝ ሲሆን ውጤት የሚሰጠው በተጨባጭ ገቢ ምርትን መተካት የሚችል 50 በመቶ እና በንግድ ሥራ ዕቅዱ ወይም የፕሮጀክት ሀሳቡ ላይ ያስቀመጠው የተኪ ምርት መጠን ደግሞ 50 በመቶ የሚያዝ ሆኖ የሁለቱ አማካይ ውጤት የመጨረሻ ውጤት ይሆናል፣

ለ) በብረታ ብረት እና እንጨት ውጤቶች የተሰማሩ 60 በመቶና በላይ ተኪ ምርት የሚያመርቱ ወይም በከፊል ያለቀለት ምርት አምርተው ተኪ ምርት ለሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት 50 በመቶና በላይ የሚያቀርቡ ከሆነ 10 ነጥብ እንዲያገኙ ይደረጋል፣

ሐ) በኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት ንዑስ ዘርፎች የተሰማሩ 50 በመቶና በላይ ተኪ ምርት የሚያመርቱ ወይም በከፊል ያለቀለት ምርት አምርተው ተኪ ምርት ለሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት 50 በመቶና በላይ የሚያቀርቡ ከሆነ 10 ነጥብ ያገኛሉ፣

መ) በጨርቃጨርቅ፣ አልባሳትና የቆዳ ውጤቶች የተሰማሩ 40 በመቶና በላይ ተኪ ምርት የሚያመርቱ ወይም በከፊል ያለቀለት ምርት አምርተው ተኪ ምርት ለሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት 50 በመቶና በላይ የሚያቀርቡ ከሆነ 10 ነጥብ እንዲያገኙ ይደረጋል፣

ሠ) በአግሮ-ፕሮሰሲንግ፣ ምግብና ፋርማሲዩቲካል ንዑስ ዘርፍ የተሰማሩ 30 በመቶና በላይ ተኪ ምርት የሚያመርቱ ወይም በከፊል ያለቀለት ምርት አምርተው ተኪ ምርት ለሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት 50 በመቶና በላይ የሚያቀርቡ ከሆነ 10 ነጥብ እንዲያገኙ ይደረጋል፣

ረ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ስር ከተዘረዘሩት ከከፍተኛ ነጥብ በታች ተኪ ምርት ለሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚሰጠው ነጥብ የከፍተኛውን መነሻ በማድረግ በመቶኛ እየተሰላ የሚሰጥ ይሆናል፣

ሰ) ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (2) ስር የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው ሁለቱንም ተግባራት በአንድ ላይ የሚያከናውን አምራች ኢንዱስትሪ ከሆነ ስሌቱ በሁለቱም ተሰርቶ ይደመርና ከከፍተኛው ነጥብ ከበለጠ ከፍተኛውን ነጥብ ብቻ ይሰጠዋል፣

ለምሳሌ፡- አንድ በጨርቃጨርቅ ንዑስ ዘርፍ የተሰማራ አምራች ኢንዱስትሪ በተግባራዊ ሂደቱ ሲመዘን ምንም ተኪ ምርት የማያመርት ከሆነ ዜሮ ነጥብ ይሰጠዋል፡፡ ነገር ግን ባቀረበው የንግድ ሥራ ዕቅድ ወይም የፕሮጀክት ሀሳብ 30 በመቶ ምርቱ ገቢ ምርትን የሚተካ መሆኑን ቢያሳይ (30/40)*10 = 7.5 ይሆናል፡፡ ኢንዱስትሪው የሚያገኘው ጠቅላላ ውጤት (0 +7.5)/2 = 3.75 ነጥብ ይሰጠዋል ማለት ነው፡፡

(ሸ) በከፊል ያለቀለት ምርት አምርተው ተኪ ምርት ለሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት የሚያቀርቡ ከሆነ በተመሳሳይ መንገድ የሚሰራ ይሆናል፤

(3) **የሥራ ዕድል 20 በመቶ የሚይዝ ሲሆን፡-**

የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቱ ከየንዑስ ዘርፉ አኳያ ሲቋቋም ሊፈጥር የሚችለው ቋሚ የሥራ ዕድል እየታየ የሚመዘን ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት፡-

ሀ) ለግምገማ የቀረበው ፕሮጀክት 100 እና በላይ ለሆኑ ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል የሚፈጥር ከሆነ 20 ነጥብ ይሰጣል፣

ለ) ለግምገማ የቀረበው ፕሮጀክት ከ100 በታች ለሚሆኑ ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል የሚፈጥር ከሆነ የከፍተኛውን ነጥብ መነሻ በማድረግ በስሌት የሚሠራ ይሆናል፣

ሐ) ለግምገማ የቀረበው ፕሮጀክት ከ51 በታች ለሆኑ ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል የሚፈጥር ከሆነ የሚሰጥ ነጥብ አይኖርም፤

(4) **የኢንቨስትመንት ካፒታል 25 ነጥብ የሚይዝ ሆኖ**

ሀ) ለአግሮ-ፕሮሰሲንግ፣ ምግብና ፋርማሲዮቲካል ንዑስ ዘርፍ ፕሮጀክቶች፦

1. የኢንቨስትመንት ካፒታሉ 100 ሚሊዮን ብር እና በላይ ያስመዘገበ ከሆነ 25 ነጥብ ይሠጣል፣
2. የኢንቨስትመንት ካፒታሉ ከ100 ሚሊዮን ብር በታች ከሆነ የከፍተኛውን ነጥብ መነሻ በማድረግ በስሌት የሚሠራ ይሆናል፣

ለ) ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች ንዑስ ዘርፍ ፕሮጀክቶች፦

1. የኢንቨስትመንት ካፒታሉ 120 ሚሊዮን ብር እና በላይ ያስመዘገበ ከሆነ 25 ነጥብ ይሰጣል፣
2. የኢንቨስትመንት ካፒታሉ ከ120 ሚሊዮን ብር በታች ከሆነ የከፍተኛውን ነጥብ መነሻ በማድረግ በስሌት የሚሠራ ይሆናል፣

ሐ) በእንጨትና ብረታብረት ንዑስ ዘርፍ የሚቀርቡ ፕሮጀክቶች፦

በብረታብረትና የብረታብረት ውጤቶች ለሚሰማሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች፦

1. የኢንቨስትመንት ካፒታሉ 150 ሚሊዮን ብር እና በላይ ያስመዘገበ ከሆነ 25 ነጥብ ይሰጣል፣
2. የኢንቨስትመንት ካፒታሉ ከ150 ሚሊዮን ብር በታች ከሆነ የከፍተኛውን ነጥብ መነሻ በማድረግ በስሌት የሚሠራ ይሆናል፣

በእንጨትና የእንጨት ውጤቶች ማቀነባበር ለሚሰማሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች፦

3. የኢንቨስትመንት ካፒታሉ 120 ሚሊዮን ብር እና በላይ ያስመዘገበ ከሆነ 25 ነጥብ ይሠጣል፣
4. የኢንቨስትመንት ካፒታሉ ከ120 ሚሊዮን ብር በታች ከሆነ የከፍተኛውን ነጥብ መነሻ በማድረግ በስሌት የሚሠራ ይሆናል፣

መ) የኬሚካል እና ኮንስትራክሽን ግብዓት አምራች ንዑስ ዘርፍ ፕሮጀክቶች፦

ኮንስትራክሽን ግብዓት አምራች ንዑስ ዘርፍ ፕሮጀክቶች፦

1. የኢንቨስትመንት ካፒታሉ 120 ሚሊዮን ብር እና በላይ ያስመዘገበ ከሆነ 25 ነጥብ ይሠጣል፣
2. የኢንቨስትመንት ካፒታሉ ከ120 ሚሊዮን ብር በታች ከሆነ የከፍተኛውን ነጥብ መነሻ በማድረግ በስሌት የሚሠራ ይሆናል፣

ኬሚካል አምራች ንዑስ ዘርፍ ፕሮጀክቶች፦

3. የኢንቨስትመንት ካፒታሉ 120 ሚሊዮን ብር እና በላይ ያስመዘገበ ከሆነ 25 ነጥብ ይሠጣል፣
4. የኢንቨስትመንት ካፒታሉ ከ120 ሚሊዮን ብር በታች ከሆነ የከፍተኛውን ነጥብ መነሻ በማድረግ በስሌት የሚሠራ ይሆናል፣
5. ይሁን እንጅ በሁለቱም መመዘኛዎች ላይ ከብር 10,000,001 /አስር ሚሊዮን አንድ ብር/ በታች የሀብት መጠን ያለው ከሆነ ነጥብ አያገኝም፣

(5) የአገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ አጠቃቀም 10 ነጥብ የሚይዝ ሲሆን፡-

በሀገር ውስጥ የሚገኝ የተፈጥሮ ሀብትንና የግብርናውን ምርት ውጤት እንዲሁም ሌሎች የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎችን መጠቀም የሚመለከት ሆኖ፦

ሀ) ዋና የጥሬ ዕቃ ግብዓታቸው መገኛ 75 በመቶና በላይ ከአገር ውስጥ ከሆነ 10 ነጥብ ይሰጠዋል፣

ለ) ዋና የጥሬ ዕቃ ግብዓታቸው መገኛ ከ75 በመቶ በታች ከአገር ውስጥ ከሆነ የከፍተኛውን ነጥብ መነሻ በማድረግ በስሌት የሚሠራ ይሆናል፣

(6) የቴክኖሎጅ ዕድገት አስተዋጽኦ 10 ነጥብ ሆኖ፦

ሀ) የሚጠቀመው የኢንዱስትሪ ቴክኖሎጅ ለአገራችን አዲስ ከሆነ 3 ነጥብ፣

ለ) ቴክኖሎጅው አዲስ ባይሆንም ቴክኖሎጂው ምርትን በተሻለ ጥራትና ፍጥነት ለማምረት የሚያስችል ከሆነ 1 ነጥብ፣

ሐ) የማምረት አቅሙ ከፍተኛ ከሆነ 3 ነጥብ፣

መ) የሚጠቀመው የኃይል መጠን አነስተኛ ከሆነ 2 ነጥብ፤

ሠ) ከአካባቢው ባሕልና እሴት ጋር የማይቃረን ከሆነ 1 ነጥብ፤

(7) የአምራች ኢንዱስትሪዎች ትስስር ያለው 15 ነጥብ፡-

ከፊትም ሆነ ከኋላ በተቀባይነትና በመጋቢነት ወይም ከሁለቱ በአንዱ ትስስር ያላቸው የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች እንደ ትስስር ስፋታቸው ተመዝነው ውጤት የሚሰጣቸው ሲሆን፦

ሀ) የሌሎችን ኢንዱስትሪ ምርት በግብዓትነት የሚጠቀምና ያመረተውን ምርት ለሌሎች ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት የሚያቀርብ ከሆነ 15 ነጥብ፣

ለ) የሌሎችን ኢንዱስትሪ ምርት በግብዓትነት የሚጠቀም ከሆነ 12 ነጥብ፣

ሐ) ያመረተውን ምርት ለሌሎች ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት የሚያቀርብ ከሆነ 10 ነጥብ፣

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) ከፊደል ተራ ሀ) እስከ ሐ) ከተዘረዘሩት ውጭ ያለ ኢንዱስትሪ ነጥብ አይሰጠውም፤

(8) በማኅበር ለተደራጁ የሴቶች ቁጥር ከ25-49 በመቶ ከሆነ ተጨማሪ 3 ነጥብ ለማበረታቻነት ይሰጣል፣

(9) በሴቶች ባለቤትነት ወይም በማኅበር ለተደራጁ የሴቶች ቁጥር 50 በመቶና በላይ ከሆነ እንደሴቶች ባለቤትነት ተቆጥሮ ተጨማሪ 5 ነጥብ ለማበረታቻነት ይሰጣል፣

(10) ሆኖም በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (9) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በውድድሩ እኩል ነጥብ ካስመዘገቡ፡-

ሀ) ውድድሩ በወንድና በሴት መካከል ከሆነ ቅድሚያ ለሴት ይሠጣል፣

ለ) ውድድሩ በተመሳሳይ ጾታ ከሆነ ባለው የፕሮጀክቱ ፋይዳ ይመረጣል፤

6. የመሥሪያ ቦታ /መሬት/ መጠን አወሳሰን

(1) ለግምገማ የሚቀርበው የፕሮጀክት ሀሳብ አዋጭነቱ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳው ታይቶ የተሻለና ቅድመ-ሁኔታዎችን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ለውድድር ይመለመላል፤

(2) የመሥሪያ ቦታ /መሬት/ እንዲሰጠው ጥያቄ ለሚያቀርብ ፕሮጀክት የሚሰጥ የቦታ መጠን ባለሃብቱ በሚያቀርበው ፕላንትና ማሽን ሌይ አውት (Plant and Machine Layout) መሠረት ተገምግሞ የሚወሰን ይሆናል፤

(3) በማስረጃነት የሚቀርበው ማሽን ሌይ አውት ከፕሮፎርማ ወይም ከማሽን አምራች ካንፓኒው የመረጃ መረብ ሲሆን ፕላንት ሌይ አውቱ ደግሞ በፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ ላይ በሚገለጸው ዝርዝር ሀሳብ ይሆናል።

ክፍል ሦስት
የማለፊያ ውጤትን ስለመወሰን እና ይፋ ስለማድረግ

7. የማለፊያ ውጤትን ስለመወሰን

በዚህ መመሪያ የሚገመገሙ ፕሮጀክቶች የማለፊያ ውጤት፡-

(1) ባህር ዳር፣ ጎንደር፣ ደብረ-ብርሃን፣ ቡሬ፣ ደብረ-ማርቆስ፣ ቱለፋና ኮምቦልቻ ከተሞች ለሚገቡ ፕሮጀክቶች የማለፊያ ነጥብ 70% ይሆናል፤

(2) ደብረ-ታቦር፣ እንጅባራ፣ ደሴ፣ ከሚሴ፣ ገንዳ ዉሃ፣ ወልዲያ እና ፍኖተ-ሠላም ከተሞች ለሚገቡ ፕሮጀክቶች የማለፊያ ነጥብ 60% ይሆናል፤

(3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ከተጠቀሱት ከተሞች ውጭ ያሉት ከተሞችና ወረዳዎች 50% ይሆናል፡፡

8. ውጤትን ይፋ ማድረግ

(1) ለቀረበው ፕሮጀክት የሚያስፈልገው የመሬት መጠን ወይም የመሥሪያ ቦታ በኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋም ገምጋሚ ኮሚቴ ተገምግሞ በጽ/ቤቱ/ በመምሪያው ማኔጅመንት ከፀደቀ በኋላ ለከተማ ከንቲባ/ምክትል ከንቲባ ወይም ለዞን/ለወረዳ ዋና አስተዳዳሪ/ምክትል አስተዳዳሪ ወይም በእነዚህ አካላት ሕጋዊ ውክልና የተሰጠው አካል እንዲያፀድቀው በማድረግ የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋምም የፀደቀውን ውጤት በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ ይፋ ያደርጋል፤

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሮጀክቱ የሚገመገመው በክልል ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ደረጃ ከሆነ በክልል ገምጋሚ ኮሚቴ ተገምግሞ በቢሮው ከፀደቀ በኋላ የፀደቀውን ውጤት በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ይፋ ያደርጋል፤

(3) ውጤቱ ይፋ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ለ5 ተከታታይ የሥራ ቀናት የሚቆይ ይሆናል፤

(4) የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋም ውጤቱን በማስታወቂያ ከገለጸበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5 የሥራ ቀናት ውስጥ ምንም ቅሬታ ካልቀረበ የተወሰነለትን የመሬት መጠን ወይም የመሥሪያ ቦታ ለባለሀብቱ ያስተላልፋል፡፡

ክፍል አራት

ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የመሥሪያ ቦታ/መሬት/ ዝግጅት፣ በክላስተር ስለማደራጀት እና የዘርፍ ለውጥ ስለመፍቀድ

9. ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የመሥሪያ ቦታ/መሬት/ ዝግጅት

(1) ቢሮው የገጠርና የከተማ ማስተር ፕላኑን ታሳቢ በማድረግ ለኢንዱስትሪ መንደሮች /ፓርኮች/፣ ለክላስተር ማእከላት፣ ለተቀናጀ ኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ ከኢንዱስትሪ መንደርና ፓርክ ውጭ ለሚገቡ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚዉል የመሥሪያ ቦታ/መሬት መለየትና በሳይት ፕላን የማመላከት ሥራ ይሠራል፤

(2) በቢሮው የተለየዉ ቦታ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ተስማሚ ሳይሆን ሲቀር እና የቦታ ምደባ ለዉጥ የሚያስፈልገዉ ከሆነ ከሚመለከተዉ ተቋም ጋር በመነጋገር ለዉጥ ያደርጋል፤

(3) በገጠርና በከተማ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲዉል የተለየዉ ቦታ በቂ ካልሆነ የወደፊት እድገትን ታሳቢ በማድረግ የኢንዱስትሪዎችን ስብጥርና ትስስር ግምት ዉስጥ በማስገባትና ከዘላቂነት አኳያ እየታየ ለተለያዩ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲዉል ተደርጎ ቦታ ይመደባል፣ የቦታ አጠቃቀም ፕላንም ይዘጋጃል፤

(4) ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የተለየዉ ቦታ ከወደፊት እድገት ጋር የሚጣጣም፣ ሁሉን አቀፍ የተቀናጀ ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል እንዲሁም ዉጤታማና ቀልጣፋ የመሠረተ-ልማት አገልግሎቶችን ለመዘርጋት እንዲመች ሆኖ ይደራጃል፤

(5) ለአምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲዉል በሳይት ፕላን የተመላከተዉን ቦታ የሚመለከተዉ መሬት አቅራቢ ተቋም የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ አዘጋጅቶ ለቢሮው ይሰጣል፤

(6) ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የተመደቡ ቦታዎችን ቢሮው ከ3ተኛ ወገን ነጻ በማድረግ እስከ መዳረሻቸዉ ድረስ መሠረታዊ የሆኑ መሠረተ-ልማቶችን (መንገድ፣ መብራት፣ ዉሃ እና ቴሌ ኮሚኒኬሽን) እንዲሟሉ ያደርጋል።

10. አምራች ኢንዱስትሪዎችን በክላስተር ማደራጀት

(1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 መሠረት ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የተለየዉን ቦታ በየንዑስ ዘርፎች በክላስተር እንዲደራጅ እና ዝርዝር ፕላን እንዲዘጋጅለት ይደረጋል፤

(2) በአንድ አካባቢ የሚመደቡ ኢንዱስትሪዎች ተመሳሳይነት ያላቸው ወይም የግብዓትና የምርት ውጤት ቅብብሎሽ ላላቸው ሊሆን ይገባል፤

(3) በአንድ አካባቢ ሁለትና ከዚያ በላይ የኢንዱስትሪ ፓርክ ሳይቶች ካሉ ከፍተኛ ብክለት ያላቸውንና በተነጻጻሪ ዝቅተኛ ብክለት ያላቸውን በመለያየት እንዲደራጁ ይደረጋል፤

(4) ተመሳሳይነት ወይም ግንኙነት የሌላቸው ኢንዱስትሪዎች በአንድ ቦታ ሊመደቡ የሚችሉት አንዱ ለሌላው የተፈጥሮና ማኅበራዊ ብክለት /Enviromental and Social Impact/ የማያስከትልና የምርት ሂደቱን የማያስተጓጉል ሲሆንና ተጽእኖውን ሊከላከል የሚችል (የተጽእኖ ማቅለያ) ሲዘጋጅ ነው፤

(5) ከፍተኛ ጭስና ብናኝ ያላቸው ኢንዱስትሪዎች ከንፋስ አቅጣጫ በተቃራኒ ጫፍ መሆን ያለባቸው ሲሆን ከፍተኛ ፍሳሽ የሚለቁ ኢንዱስትሪዎች ደግሞ በፓርኩ ዝቅተኛ ወይም ተዳፋት ወዳለው አቅጣጫ ይደራጃሉ፤

(6) ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ ወይም ክላስተር ማዕከላት ሊገቡ የማይችሉ በተለያዩ ዘርፎች ማቀነባበር (ቆዳ፣ ሲሚንቶ፤ ወ.ኃ) የተሰማሩ ፕሮጀክቶች በዚህ መመሪያ የሚመለመሉ ሁኖ ከሁሉ-ገብ ኢንዱስትሪ ፓርክና ክላስተር ማዕከላት ውጭ በሆነ ኢንዱስትሪ ዞን ሊስተናገዱ ይችላሉ፤

(7) ለአምራች ኢንዱስትሪ የሚሰጡ ቦታዎች ለመሬት መንሸራተት፣ ለአፈር መሸርሸር፣ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ተሸካሚ መስመር /High tension line/ በሚያልፍባቸው እና ሌሎች ፋብሪካውን ለአደጋ ሊያጋልጡ ከሚችሉ ችግሮች የራቁ መሆን አለባቸው።

11. የዘርፍ ለውጥ መፍቀድ

አንድ ፕሮጀክት ተወዳድሮ ካሸነፈ በኋላ አስገዳጅ በሆኑ ምክንያቶች የዘርፍ ለውጥ ቢያደርግ የሚያስገኘው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ታይቶ የዘርፍ ለውጥ ሊፈቀድ የሚችል ሲሆን፤ የዘርፍ ለውጥ ለማድረግ መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች፦

(1) አዲስ የቀረበው ፕሮጀክት ከዚህ በፊት ቀርቦ ከነበረው ፕሮጀክት በካፒታል፣ በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር፣ በማምረት አቅም፣ በአገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ አጠቃቀም፣ በኋልዮሽና በፊትዮሽ ኢኮኖሚያዊ ትስስር እና ኤክስፖርት በማድረግ የላቀ ሁኖ ሲገኝ፤

(2) አዲስ የሚቀርበው ፕሮጀክት በክላስተር ማዕከሉ ወይም በኢንዱስትሪ ፓርኩ ውስጥ ላሉ ፕሮጀክቶች እና ለአካባቢው አሉታዊ ተጽዕኖ የማያስከትል ከሆነ፤

(3) በአዲስ የቀረበው ፕሮጀክት ሌይ አውት ሲገመገም ከዚህ በፊት ከወሰደው ቦታ መጠን አንጻር ሲታይ ለመተግበር ቦታው በቂ ከሆነ፤

(4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተገለጸው እንዳለ ሆኖ ከዚህ በፊት ለነባሩ ፕሮጀክት የተሰጠው መሬት 1000 ካ.ሜ እና በላይ ትርፍ ቦታ ካለው ትርፍ ቦታውን በራሱ ወጪ ለማጽዳት እና ወደ መሬት ባንክ ለመመለስ ፈቃደኛ ከሆነ፤

(5) በግንባታ ላይ የሚገኝ ፕሮጀክት የዘርፍ ለውጥ ጥያቄ የሚያቀርበው ቀድሞ በያዘው የግንባታ ውል መሰረት እየገነባ ያለ እንዲሁም ቀሪውን ግንባታ ቀድሞ በተያዘለት የጊዜ ገደብ የሚያጠናቅቅ ከሆነ፤

(6) ግንባታ ያጠናቀቀ ፕሮጀክት ወይም ከዚህ ቀደም በማምረት ላይ የነበረ አምራች ኢንዱስትሪ የዘርፍ ለውጥ ጥያቄ ሊያቀርብ የሚችለው አዲሱን ፕሮጀክት ከስድስት ወራት እስከ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ ማምረት ለማስገባት ውለታ የሚገባ ከሆነ፤

(7) በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩትን ቅድመ-ሁኔታዎች አሟልቶ ሲገኝ የዘርፍ ለውጥ ጥያቄው በወረዳ/ከተማ የቢሮው መዋቅር ፕሮጀክት ገምጋሚ ኮሚቴ ቀርቦ ከታዬ በኋላ የውሳኔ አስተያየቱን ለዞኑ መምሪያ ይልካሉ፤

(8) የዞኑ የማኔጅመንት አካል የወረዳዉን/የከተማዉን እና የራሱን የዉሳኔ አስተያየት በመጨመር ለዘርፍ ለውጥ የቀረበውን አዲስ የፕሮጀክት ሰነድ ወደ ቢሮው በመላክ በቢሮ ደረጃ እየተረጋገጠ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል።

ክፍል አምስት

ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የመሥሪያ ቦታ /መሬት/ ማስተላለፍ፣ ወደ ትግበራ ማስገባት፣ እርምጃ አወሳሰድ እና ቅሬታን ማስተናገድ

12. የመሥሪያ ቦታ /መሬት/ ማስተላለፍ እና ወደ ትግበራ ማስገባት

(1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 በተገለጹት የመመልመያ መስፈርት መሠረት ተገምግሞ ያለፈ ፕሮጀክት መሬት/ቦታ ይተላለፍለታል፤

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተሰጠዉን መሬት ከሚመለከተዉ ተቋም የሊዝ ዉል በመዉሰድ ካርታና ፕላን በስሙ በማሰራት በ1 ወር ጊዜ ዉስጥ እንዲያጠናቅቅ ያደርጋል፤

(3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ካርታና ፕላን የተሠራለት ፕሮጀክት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተሻሻለዉ የከተማ ቦታን በሊዝ ለማስተዳደር የወጣዉ ደንብ ቁጥር 103/2004 አንቀጽ 36 ንኡስ አንቀጽ (1) መሠረት ከ9 ወር ባልበለጠ ጊዜ ዉስጥ የግንባታ ፈቃድ እንዲያወጣ ይደረጋል፤

(4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የግንባታ ፈቃድ የተሰጠዉ ፕሮጀክት የሊዝ ዉል ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ ለመካከለኛ ግንባታ በ12 ወራት፤ ለከፍተኛ ግንባታ በ18 ወራት ዉስጥ ግንባታዉን እንዲጀምር ይደረጋል፤

(5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የግንባታ ፈቃድ የተሰጠዉ ፕሮጀክት ለመካከለኛ ግንባታ 24 ወራት /ሁለት ዓመት/፤ ለከፍተኛ ግንባታ 36 ወራት /3 ዓመት/ግንባታዉን እንዲያጠናቅቅ የሚደረግ ሆኖ ግንባታዉን በወቅቱ ያላጠናቀቀዉ

ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች መሆኑን ቢሮው በማስረጃ ሲያረጋግጥ ተጨማሪ እስከ አንድ ዓመት ጊዜ ተሰጥቶት እንዲያጠናቅቅ ይደረጋል፡፡

(6) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (5) የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው ግንባታውን በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ በማጠናቀቅ ምርት ወደ ማምረት እንዲገባ ይደረጋል፡፡

13. የመስሪያ ቦታ /መሬት/ ወስደው በውላቸው መሠረት ወደ ትግበራ በማይገቡ ባለሀብቶች ላይ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች፡-

(1) ቢሮው የመሥሪያ ቦታ /መሬት/ የሰጣቸውን የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ሙሉ መረጃ አደራጅቶ በመያዝ ለድጋፍና ክትትል ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል፤

(2) በአንቀጽ 12 ከንዑስ አንቀጽ (2) እስከ (5) የተገለጹትን የግንባታ ደረጃዎች ሂደት ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

(3) በአንቀጽ 12 ከንዑስ አንቀጽ (2) እስከ (5) በተገለጹት የግንባታ ጊዜ ገደቦች መሠረት ወደ አፈጻጸም ያልገቡ ፕሮጀክቶች፡-

ሀ) የግንባታ ጊዜው ከማለቁ በፊት አንድ ወር ቀደም ብሎ የፕሮጀክቱን ባለቤት ወይም ሕጋዊ ዉክልና ለተሰጠዉ አካል ቢሮው የቃል ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፣

ለ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) ፊደል ተራ ሀ) መሠረት የተሰጠዉን የቃል ማስጠንቀቂያ ተግባራዊ ካላደረገ የግንባታ ጊዜው በተጠናቀቀ በ3ኛው ወር መጨረሻ ላይ ቢሮው የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ በአድራሻው ወይም በአካባቢዉ በሚገኝ የህዝብ ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ ግዴታዉን እንዲያዉቀዉ ያደርጋል፣

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) ፊደል ተራ ለ) መሠረት የተሰጠዉን የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተግባራዊ ካላደረገ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በተሰጠው በ3ኛው ወር መጨረሻ ላይ ቢሮው የተሰጠዉን ካርታ እንዲመክንና መሬቱም ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ በማድረግ ለሚመለከተዉ ተቋም የማሳወቅ ሥራ በመሥራት ለሌላ አልሚ ባለሃብት እንዲተላለፍ ያደርጋል፤

(4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከፊደል ተራ ሀ) እስከ ሐ) የተገለጸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሃብቱ በተሰጠዉ መሬት ላይ ግንባታ ጀምሮ ያቋረጠ (ያላጠናቀቀ)፣ ግንባታ ሙሉ በሙሉ ያጠናቀቀና ማሽን አስገብቶ በወቅቱ ወደ ማምረት ያልገባ እንዲሁም ምርት ጀምሮ ያለበቂ ምክንያት ያቋረጠ ከሆነ ከመሬት በላይ ያለዉን የንብረት ግምት በሚመለከተዉ ተቋም ተሠርቶ አዲስ የሚገባዉ ባለሃብት ግምቱን እንዲፈጽም በማድረግ የሚተላለፍ ሲሆን መሬቱን ተረክቦ ባለማልማቱ ለመንግሥትና ለህዝብ ያሳጣዉን ጥቅም ታሳቢ በማድረግ 10 ፐርሰንት ቅጣት እንዲከፍል የሚደረግ ይሆናል፡፡

14. ቅሬታን ስለማስተናገድ

(1) በፕሮጀክቶች ምልመላ ላይ የሚነሳን ቅሬታ ስለማስተናገድ፦

ሀ) በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለመሰማራት የሚቀርቡ ፕሮጀክቶች በየደረጃው ባለው የቢሮው መዋቅር እየቀረቡ የሚገመገሙ ይሆናል፤

ለ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 በተገለጸው መሠረት ውጤቱ በማስታወቂያ ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5 የሥራ ቀናት ውስጥ በወረዳ እና በከተማ አስተዳደር የቢሮው መዋቅር /ጽሕፈት ቤት/ ዉሳኔ ያልረካ አካል ካለ ቅሬታውን ለዞን መምሪያ ማቅረብ ይችላል፣ ቅሬታው የቀረበለት መምሪያም ቅሬታዉን አይቶ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ዉሳኔ ይሰጣል፣

ሐ) በመምሪያዉ ዉሳኔ ያልረካ አካል ቅሬታውን በ7 የሥራ ቀናት ዉስጥ ለቢሮው ገምጋሚ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል፣ ቅሬታ የቀረበለት የቢሮው ገምጋሚ ኮሚቴም ቅሬታዉን አይቶ በ10 የስራ ቀናት ዉስጥ የዉሳኔ አስተያየት ለቢሮዉ ያቀርባል፤

መ) በሪጅዮ-ፖሊታን ከተማ እንዲሁም በዞን መምሪያ ደረጃ በተገመገሙ ፕሮጀክቶች ያልረካ አካል ቅሬታዉን ለቢሮው ገምጋሚ ኮሚቴ በ7 የሥራ ቀናት ዉስጥ ማቅረብ ይችላል፣ ቅሬታ የቀረበለት የቢሮው ገምጋሚ ኮሚቴም ቅሬታዉን አይቶ በ10 የሥራ ቀናት ዉስጥ የዉሳኔ አስተያየት ለቢሮዉ ያቀርባል፣

ሠ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከፊደል ተራ ለ) እስከ መ) ባለዉ ውሳኔ እና በቢሮው ገምጋሚ ኮሚቴ በተገመገሙ ፕሮጀክቶች ያልረካ አካል ካለ ቅሬታውን በ7 የሥራ ቀናት ዉስጥ ለቢሮው ማቅረብ ይችላል፣ ቅሬታ የቀረበለት ቢሮም ቅሬታውን አይቶ በ15 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፣ ቢሮው የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

(2) የተነጠቀ መሬት/ቦታን አስመልክቶ ቅሬታን ስለማስተናገድ፦

ሀ) በአንቀጽ 13 ከንዑስ አንቀጽ (3) እስከ (4) በተገለጸዉ መሠረት በወረዳ /ከተማ አስተዳደር የቢሮው መዋቅር ጽሕፈት ቤት እርምጃ የተወሰደበት ፕሮጀክት /ባለሃብት/ ቅሬታ ካለዉ መሬቱ /ቦታዉ መነጠቁን በደብዳቤ ወይም በማስታወቂያ እንዲያዉቀዉ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5 የሥራ ቀናት ዉስጥ ቅሬታዉን ለወረዳ አስተዳደሪ /ም/አስተዳዳሪ ወይም ከተማ አስተዳደር ከንቲባ/ም/ከንቲባ ወይም በእነዚህ አካላት ሕጋዊ ውክልና ለተሰጠው አካል ማቅረብ ይችላል፣ ቅሬታ የቀረበለት የወረዳ አስተዳዳሪ ወይም የከተማ ከንቲባ ቅሬታዉን አይቶ በ10 የሥራ ቀናት ዉስጥ ዉሳኔ ይሰጣል፣

ለ) በወረዳ አስተዳዳሪ/ም/አስተዳዳሪ ወይም ከተማ ከንቲባ/ም/ከንቲባ ዉሳኔ ያልረካ አካል ቅሬታዉን ለዞን ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት መምሪያ ማቅረብ ይችላል፣ ቅሬታ የቀረበለት የዞን ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት መምሪያም ቅሬታዉን አይቶ በ10 የሥራ ቀናት ዉስጥ ዉሳኔ ይሰጣል፣

ሐ) በዞን ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት መምሪያ ዉሳኔ ያልረካ አካል ካለ ቅሬታዉን ለዞን አስተዳዳሪ/ም/አስተዳዳሪ ወይም በዚህ አካል ሕጋዊ ውክልና ለተሰጠው አካል በ7 ተከታታይ የስራ ቀናት ዉስጥ ማቅረብ ይችላል፡፡ ቅሬታ የቀረበለት የዞን አስተዳዳሪም ቅሬታዉን አይቶ በ10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ዉስጥ ዉሳኔ ይሰጣል፤

መ) በሪጅዮ-ፖሊታን ከተማ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት መምሪያ እርምጃ የተወሰደበት ፕሮጀክት /ባለሃብት/ ከሆነና ቅሬታ ካለዉ መሬቱ/ቦታዉ መነጠቁን በደብዳቤ ወይም በማስታወቂያ እንዲያዉቀዉ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5 ተከታታይ የሥራ ቀናት ዉስጥ ቅሬታዉን ለሪጅዮ-ፖሊታን ከተማ ከንቲባ/ም/ከንቲባ ወይም በዚህ አካል ሕጋዊ ውክልና ለተሰጠው አካል ማቅረብ ይችላል፡፡ ቅሬታ የቀረበለት የሪጅዮ-ፖሊታን ከተማ ከንቲባም/ም/ከንቲባም ቅረታዉን አይቶ በ10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ዉስጥ ዉሳኔ ይሰጣል፡፡

ሠ) በዞን አስተዳዳሪ ወይም በሪጅዮ-ፖሊታን ከተማ ከንቲባ ዉሳኔ ያልረካ አካል ካለ ቅሬታዉን ለክልሉ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ በ10 የሥራ ቀናት ዉስጥ ማቅረብ ይችላል፡፡ ቅሬታ የቀረበለት የክልል ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮም ቅሬታዉን አይቶ በ15 የሥራ ቀናት ዉስጥ ዉሳኔ ይሰጣል፣

ረ) በክልሉ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ውሳኔ ያልረካ አካል ካለ ቅሬታውን በ10 የሥራ ቀናት ዉስጥ ለክልሉ ኢንቨስትመንት ቦርድ ማቅረብ ይችላል፡፡

ክፍል ስድስት

የቢሮው መዋቅሮች፣ የገምጋሚ ኮሚቴ ተግባርና ኀላፊነት እና የገምጋሚ ኮሚቴው አደረጃጀት

15. የቢሮው መዋቅሮች ተግባርና ኀላፊነት

(1) ቢሮዉ አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ በአምራች ዘርፉ ለሚሰማሩ አነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ ሁሉ-ገብ የኢንዱስትሪ ፓርክ፣ የክላስተር ማዕከላት፣ የተቀናጀ ኢንዱስትሪ ፓርክ እና ከሁሉ-ገብ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውጭ ለሚገቡ የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች የሚያስፈልገውን የመሥሪያ ቦታ /መሬት/ ከሦስተኛ ወገኖች ይዞታ ነፃ እንዲሆን ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፣ የቦታ ካርታና ፕላን በማሠራትም ሆነ እስከ መዳረሻቸው የሚዘልቅ መሠረተ-ልማት እንዲሟላላቸው ያደርጋል፤

(2) ለአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች መስፋፋት ዘላቂ ፋይዳ ያለው የአዋጭነት ጥናትና የፕሮጀክት ትግበራ፣ ክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ቀርፆ ተግባራዊ ያደርጋል፤

(3) በገጠርም ሆነ በከተማ በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ በኩል የሚቀርቡለትን ፕሮጀክቶች ይቀበላል፣ ወደ ክላስተር ማእከላት፣ የሁሉ-ገብ ኢንዱስትሪ ፓርክ ወይም ወደ ተቀናጀ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ወይም ከሁሉ-ገብ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውጭ ሊገቡ የሚችሉትን በአይነት ይለያል፣ የፕሮጀክቶችን ፕላንት ሌይአውት ይገመግማል፣ የሚያስፈልጋቸውን የመሬት መጠን ይወስናል፤

(4) በክልሉ ውስጥ የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽንን ለማስፋፋት በየአካባቢው ያለውን የመልማት አቅም መሠረት ያደረገ የአምራች ኢንዱስትሪ ዓይነቶችን ይለያል፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ያደራጃል፣ ተፈላጊው መሠረተ-ልማት እንዲሟላላቸው ያደርጋል፤

(5) በሚመለከተው አካል ተለይቶ በተዘጋጀው የኢንዱስትሪ ቀጠና አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ይሠራል፣ የቀጠናዎቹ ወሰንና የአጠቃቀም ለውጥ በመሬት ተቋም እንዲመዘገብ ያደርጋል፤

(6) በገጠርም ሆነ በከተማ ወደ የኢንዱስትሪ ቀጠና እንዲገቡ ለተመረጡ አልሚዎች ያቀረቧቸውን ፕሮጀክቶች በመገምገምና የመሬት መጠን በመወሰን ተለይቶ የተዘጋጀውን የመሥሪያ ቦታ /መሬት/ ውል ይዞ ያስተላልፋል፣ እንዳስፈላጊነቱ የመሠረተ-ልማት ማሟላት ተግባራትን ያከናውናል፣ በውላቸው መሠረት በማያለሙት ላይ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣ መሬቱን ተመላሽ በማድረግ ለክልሉ መሬት ቢሮ እና ለፌደራል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በማሳወቅ ለሌላ አልሚ ያስተላልፋል፤

(7) በክልሉ ውስጥ በኢንቨስትመንት ሥራ የተሰማሩ ባለሀብቶችን ያበረታታል፣ ይደግፋል፣ ፈጥነው ወደ አፈጻጸም በማይገቡ ፕሮጀክቶች ላይ ደግሞ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ፈቃድ የመሰረዝና መሬት የማስመለስ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰዱ ያደርጋል፤

(8) በፕሮጀክት ሐሳባቸው ቃል የገቡትን የቴክኖሎጅ ሽግግር፣ ካፒታል እና የሥራ እድል ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይከታተላል፣ ተግባራዊ በማያደርጉት ላይ እርምጃ ይወስዳል፤

(9) ባለሀብቶች በዚህ መመሪያ ይዘት ላይ የሚኖራቸው ግንዛቤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲዳብር ግንዛቤና ስልጠና ይሠጣል፤

(10) አግባብነት ካላቸው የክልሉና የፌደራሉ መንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ለአምራች ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት እንቅፋት የሚሆኑ ማነቆዎች ተለይተው እንዲፈቱ ያደርጋል፤

(11) የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ እንዲገቡ ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በመተባበር የብድር አገልግሎት እንዲመቻችላቸው ያደርጋል፤

(12) በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ ፕሮጀክቶች ዘርፍ መቀየር አስገዳጅ ሆኖ ሲገኝ የዘርፍ ለውጥ ያደርጋል፤

(13) ለአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክት የሚያስፈልገውን የመሬት/የቦታ መጠን ለመወሰን የሚችል ገምጋሚ ኮሚቴ በዚህ መመሪያ መሠረት ይሰይማል፣ የተሰየመዉ ኮሚቴም የዘርፍ ለዉጥ ጥያቄ በሚቀርብበት ወቅት ፕሮጀክቱን እየገመገመ የዉሳኔ አስተያየት እንዲያቀርብ ያደርጋል፤

16. የፕሮጀክት ገምጋሚ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

(1) የቢሮው ገምጋሚ ኮሚቴ፦

ቡሬ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክን ጨምሮ በልዩ ሁኔታ በክልል የሚገመገሙ ከፍተኛ የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች፡-

ሀ) ጠቅላላ የኢንቨስትመንት ካፒታላቸዉ ከ250 ሚሊየን ብር በላይ ከሆነ፣

ለ) የሚፈጥሩት ቋሚ የሥራ እድል ከ100 በላይ ከሆነ፣

ሐ) በሌይ አዉቱ መሠረት የመሥሪያ ቦታ /መሬት/ መጠን ከ2 ሄክታር በላይ ከሆነ፣

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከፊደል ተራ ሀ) እስከ ሐ) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸው የጎላ እና ከ5 ሄክታር በላይ መሬት የጠየቁ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ሲቀርቡ በቢሮው በኩል እየተገመገሙ ለክልሉ ርዕሰ መስተዳደር በማቅረብ የሚፀድቁ ይሆናል፡፡

ሠ) ባለሀብቱ ወይም የፕሮጀክቱን ሰነድ ያዘጋጀው ኮንሰልታንት ወይም አማካሪ ቀርቦ ገለጻ ሊያደርግና ተፈላጊ መረጃ መስጠት የሚችል መሆን ያለበት ሲሆን የሚቀርበዉን ሌይ

አዉት በተመለከተ በዝርዝር በፕሮጀክቱ የተካተቱ ነገሮችን ማመላከትና በብሉ ፕሪንት ተሠርቶ መቅረብ መቻል አለበት፣

ረ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከፊደል ተራ ሀ) እስከ መ) በተገለጹት መስፈርቶች አሻሚ ሁኔታ ሲገጥም የኢንቨስትመንት ካፒታሉ የሚታይ ይሆናል፣

ሰ) ፕሮጀክት ለመገምገም የኮሚቴ አባላት ያልተሟሉባቸውን ዞኖችን እና ሪጅዮ-ፖሊታን ከተሞች በመለየት የባለሙያ ድጋፍ ያደርጋል፣

ሸ) የተገመገሙ ፕሮጀክቶች በዚህ መገምገሚያ መስፈርት መሠረት እየተገመገሙ ስለመሆኑ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ ያረጋግጣል፣

ቀ) ተገምግመው ላለፉ ፕሮጀክቶች የተወሰነላቸውን የመሬት መጠን ለቢሮው ያቀርባል፣

በ) በዞኖች እና ሪጅዮ-ፖሊታንት ከተሞች የሚቀርበውን የዘርፍ ለውጥ የውሳኔ አስተያየትና አዲሱን የፕሮጀክት ሰነድ በመገምገም የውሳኔ ሀሳብ ለቢሮው ያቀርባል፣

ተ) በፕሮጀክት ግምገማ እና በዘርፍ ለዉጥ አሠራር ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን በማየት የውሳኔ ሃሳብ ለቢሮው ያቀርባል፣

ቸ) በየደረጃዉ የሚደረገዉን የፕሮጀክት ግምገማ ሂደት በየጊዜዉ በመከታተል ክፍተት በተገኘበት ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣

ኀ) ከግምገማ ውጤቱ በመነሳት ጉድለትና ጥንካሬዎችን በመቀመር ትምህርት እንዲወሰድ ያደርጋል፤

(2) **የዞን ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት መምሪያ ገምጋሚ ኮሚቴ**

በመምሪያ ደረጃ የሚገመገሙ ከፍተኛ የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች፡-

ሀ) ጠቅላላ የኢንቨስትመንት ካፒታላቸዉ 90,000,001 እስከ 250 ሚሊየን ብር ከሆነ፣

ለ) የሚፈጥሩት ቋሚ የሥራ እድል 100 እና በላይ ከሆነ፣

ሐ) በሌይ አዉቱ መሠረት የመሥሪያ ቦታ /መሬት/ መጠን ከ0.5 ሄክታር በላይ እስከ 2 ሄክታር ከሆነ፣

መ) የሚቀርበዉ የፕሮጀክት ሰነድ ባለሀብቱ ወይም የፕሮጀክቱን ሰነድ ያዘጋጀው ኮንሰልታንት ወይም አማካሪ ቀርቦ ገለጻ ሊያደርግና ተፈላጊ መረጃ መስጠት የሚችል መሆን ያለበት ሲሆን የሚቀርበዉን ሌይአዉት በተመለከተ በዝርዝር በፕሮጀክቱ የተካተቱ ነገሮችን ማመላከትና በብሉ ፕሪንት ተሠርቶ መቅረብ መቻል አለበት፣

ሠ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከፊደል ተራ ሀ) እስከ ሐ) በተገለጹት መስፈርት አሻሚ ሁኔታ ሲገጥም የኢንቨስትመንት ካፒታሉ የሚታይ ይሆናል፣

ረ) በወረዳዎች/ከተሞች የተገመገሙ ፕሮጀክቶች በዚህ መገምገሚያ መስፈርት መሠረት እየተገመገሙ ስለመሆኑ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ ያረጋግጣል፣

ሰ) ፕሮጀክት ለመገምገም መዋቅር የሌለባቸውን ወረዳዎች/ከተሞችን በመለየት ፕሮጀክቶችን ይገመግማል፣ ይመዝናል፣ የመሬት አቅርቦት መጠንን ይወስናል፣ ለመዋቅሩ ማኔጅመንት ያቀርባል፤

ሸ) ፕሮጀክት ለመገምገም የገምጋሚ ኮሚቴ አባላት ያልተሟሉባቸውን ወረዳዎች/ከተሞች በመለየት የባለሙያ ድጋፍ ያደርጋል፣ ዞኑ የሚመለከተው ባለሙያ ከሌለው ከሌሎች ወረዳዎች ወይም ከተሞች ባለሙያ በመዋስ እንዲገመግሙ ያመቻቻል፤

ቀ) በወረዳዎች ወይም ከተሞች የቀረቡ የዘርፍ ለውጥ የውሳኔ አስተያየትንና የዘርፍ ለውጥ የተጠየቀበትን አዲስ ፕሮጀክት በመገምገም የራሱን የውሳኔ አስተያየትና ፕሮጀክት ፕሮፖዛሉን ጨምሮ ለቢሮው ይልካል፣

በ) በወረዳና ከተማ የሚደረገዉን የፕሮጀክት ግምገማ ሂደት በየጊዜዉ በመከታተል ክፍተት በተገኘበት ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣

ተ) ከግምገማ ውጤቱ በመነሳት ጉድለትና ጥንካሬዎችን በመቀመር ትምህርት እንዲወሰድ ያደርጋል፤

(3) የሪጂዮ-ፖሊታን ከተሞች ገምጋሚ ኮሚቴ

ወደ ሁሉ-ገብ ኢንዱስትሪ ፓርክ ወይም ከኢንዱስትሪ መንደር እና ፓርክ ዉጭ የሚቀርቡ ፕሮጀክቶችን በመመሪያው መሠረት ይገመግማል፣ የሚገመገሙ ፕሮጀክቶችም፦

ሀ) ጠቅላላ የኢንቨስትመንት ካፒታላቸዉ ከ10,000,001 እስከ 250 ሚሊየን ብር የሆኑ ፕሮጀክቶች፣

ለ) ጠቅላላ የሚፈጥሩት ቋሚ የሥራ እድል 51 እና በላይ ከሆነ፣

ሐ) በሌይ አዉቱ መሠረት የመሥሪያ ቦታ /መሬት/ መጠን እስከ 2 ሄክታር ከሆነ፣

መ) የሚቀርበዉ የፕሮጀክት ሰነድ ባለሀብቱ ወይም የፕሮጀክቱን ሰነድ ያዘጋጀው ኮንሰልታንት ወይም አማካሪ ቀርቦ ገለጻ ሊያደርግና ተፈላጊ መረጃ መስጠት የሚችል መሆን ያለበት ሲሆን የሚቀርበዉ ሌይ ዉትን በተመለከተ በዝርዝር በፕሮጀክቱ የተካተቱ ነገሮችን ማመላከትና በብሉ ፕሪንት ተሠርቶ መቅረብ መቻል አለበት፤

ሠ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከፊደል ተራ ሀ) እስከ ሐ) በተገለጹት መስፈርቶች አሻሚ ሁኔታ ሲገጥም የኢንቨስትመንት ካፒታሉ የሚታይ ይሆናል፣

ረ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከፊደል ተራ ሀ) እስከ ሐ) የተገለጹትን ቅድመ-ሁኔታዎች አሟልተው ወደ ሁሉ-ገብ ኢንዱስትሪ ፓርክ ወይም ኢንዱስትሪ መንደር እና

ፓርክ ዉጭ የሚገቡ ፕሮጀክቶች የሚያስፈልጋቸውን የመሬት መጠን የውሳኔ ሃሳብ ለመዋቅሩ ማኔጅመንት ያቀርባል፣

ሰ) ከግምገማ ውጤቱ በመነሳት ጉድለትና ጥንካሬዎችን በመቀመር ትምህርት እንዲወሰድ ያደርጋል፣

ሸ) በባለሀብቶች የሚቀርቡ አስገዳጅ የዘርፍ ለውጥ ጥያቄዎችን በመገምገም የውሳኔ አስተያየትና አዲሱን የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ጨምሮ ለቢሮው ይልካል፤

(4) በወረዳ/ከተማ አስተዳደር ገምጋሚ ኮሚቴ፦

ወደ ሁለ-ገብ ኢንዱስትሪ ፓርክ የሚገቡ ወይም ከኢንዱስትሪ መንደርና ፓርክ ዉጭ የሚቀርቡ ፕሮጀክቶችን በመመሪያው መሠረት የሚገመግም ሲሆን የሚገመገሙ ፕሮጀክቶችም፡-

ሀ) ጠቅላላ የኢንቨስትመንት ካፒታላቸዉ ከ10,000,001 እስከ 90 ሚሊየን ብር የሆነ፣

ለ) የሚፈጥሩት ቋሚ የሥራ እድል 51 እና በላይ የሆነ፣

ሐ) በለይ አዉቱ መሠረት የመሥሪያ ቦታ /መሬት/ መጠን እስከ 0.5 ሄክታር የሆነ፣

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ከፊደል ተራ ሀ) እስከ ሐ) በተገለጹት መስፈርቶች አሻሚ ሁኔታ ሲገጥም የኢንቨስትመንት ካፒታሉ የሚታይ ይሆናል፣

ሠ) ባለሀብቱ ወይም የፕሮጀክቱን ሰነድ ያዘጋጀው ኮንሰልታንት ወይም አማካሪ ቀርቦ ገለጻ ሊያደርግና ተፈላጊ መረጃ መስጠት የሚችል መሆን ያለበት ሲሆን የሚቀርበዉን ሌይ አዉት በተመለከተ በዝርዝር በፕሮጀክቱ የተካተቱ ነገሮችን ማመላከትና በብሉ ፕሪንት ተሠርቶ መቅረብ መቻል አለበት፣

ረ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ከፊደል ተራ ሀ) እስከ ሐ) የተገለጹትን ቅድመ-ሁኔታዎች አሟልተው ወደ ሁለ-ገብ ኢንዱስትሪ ፓርክ ወይም ከኢንዱስትሪ መንደር እና ፓርክ ዉጭ የሚገቡ ፕሮጀክቶች የሚያስፈልጋቸውን የመሬት መጠን የውሳኔ ሃሳብ ለተቋሙ ማኔጅመንት ያቀርባል፣

ሰ) ከግምገማ ውጤቱ በመነሳት ጉድለትና ጥንካሬዎችን በመቀመር ትምህርት እንዲወሰድ ያደርጋል፣

ሸ) በባለሀብቶች የሚቀርቡ አስገዳጅ የዘርፍ ለውጥ ጥያቄዎችን በመገምገም የውሳኔ አስተያየትና አዲሱን የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ጨምሮ ለመምሪያው ይልካል፤

17. የፕሮጀክት ገምጋሚ ኮሚቴ አደረጃጀት

(1) በክልል ደረጃ፦

ሀ) የኢንዱስትሪ ዞንና አካባቢ እንክብካቤ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ------------------ ሰብሳቢ፣

ለ) ከኢንዱስትሪ ዞንና አካባቢ እንክብካቤ ዳይሬክቶሬት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ድጋፍና ክትትል ባለሙያ -- አባል እና ፀሐፊ፣

ሐ) የሚመለከተው የኢንዱስትሪ ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር -------------------- አባል፣

መ) ከኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ የሚመለከተው ኢንዱስትሪ መሀንዲስ/ባለሙያ……... አባል፣

ሠ) ከኢንዱስትሪ ዞንና አካባቢ እንክብካቤ ዳይሬክቶሬት ሲቪል መሀንዲስ ------------- አባል፤

(2) በዞንና ሪጅዮ ፖሊታን ከተማ፦

ሀ) የኢንቨስትመንት ማስፋፊያና ኢንዱስትሪ ዞን ልማት ቡድን መሪ --------------- ሰብሳቢ፣

ለ) የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ድጋፍና ክትትል ባለሙያ --------------- አባል እና ፀሐፊ፣

ሐ) የኢንዱስትሪ ልማት ቡድን መሪ ---አባል፣

መ) ከኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ የሚመለከተው ኢንዱስትሪ መሀንዲስ/ባለሙያ……... አባል፣

ሠ) ከኢንቨስትመንት ማስፋፊያና ኢንዱስትሪ ዞን ልማት ቡድን ሲቪል መሀንዲስ --- አባል፤

(3) በወረዳ/ከተማ አስተዳደር፦

ሀ) የኢንቨስትመንት ማስፋፊያና ኢንዱስትሪ ዞን ልማት ቡድን መሪ --------------- ሰብሳቢ፣

ለ) የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ድጋፍና ክትትል ባለሙያ ----------------- አባል እና ፀሐፊ፣

ሐ) የኢንዱስትሪ ልማት ቡድን መሪ -- አባል፣

መ) ከኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ የሚመለከተው ኢንዱስትሪ መሀንዲስ/ባለሙያ……….አባል፣

ሠ) ከኢንቨስትመንት ማስፋፊያና ኢንዱስትሪ ዞን ልማት ቡድን ሲቪል መሀንዲስ --- አባል፤

ክፍል ሰባት
መብቶች እና ግዴታዎች

18. መብቶች

(1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንኡስ አንቀጽ (12) የተገለጸዉን ሙሉ በሙሉ የሚያሟሉ ከሆነ የባንክ ትራንዝአክሽን እና ዝግ አካዉንት ያለመጠየቅ፤

(2) የመሬት ካሳ ከፍለዉ ወደ ሁለ-ገብ ኢንዱስትሪ መንደር/ፓርክ ወይም ከሁለ-ገብ ኢንዱስትሪ መንደር/ፓርክ ውጭ የሚገቡ ባለሃብቶች ከባንክ ትራንዝአክሽን ዉጭ ዝግ አካዉንት እንዲያስይዙ ያለመጠየቅ፤

(3) የመሬት ካሳ ከፍለዉ የሚገቡ ፕሮጀክቶች የከፈሉት የመሬት ካሳ ገንዘብ የሊዝ ክፍያዉን የሚሸፍን ሆኖ እስከተገኘ ድረስ የሊዝ ክፍያ ሳይጠየቁ የመስተናገድ መብቶች አሏቸው።

19. ግዴታዎች

(1) ባለሃብቱ መሬቱን ከተረከበ በኋላ የፕሮጀክቱን አፈፃፀም ለመከታተል፣ ለመደገፍና ለመቆጣጠር ለሚሰማሩ የተቋሙ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የሚያስፈልጉ ማናቸውንም መረጃዎች የመስጠት፣

(2) ባለሃብቱ መሬቱን ከተረከበ በኋላ የፕሮጀክቱን አፈፃፀም በግንባታ ዕቅዱ መሠረት በየሶስት ወሩ ሳይቆራረጥ በየደረጃው ለሚገኙ የቢሮው መዋቅሮች እና የፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ባለበት ከተማ ለፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ሪፖርት የማድረግ፤

(3) ምርታቸውን ወደ ውጭ አገር እንደሚልኩ ውል ገብተው ቦታ የተረከቡ ባለሀብቶች ወይም ምርታቸውን ወደ ውጭ ለሚልኩ ፋብሪካዎች በግብዓትነት የሚያቀርቡ ባለሀብቶች በገቡት ውል መሠረት እየፈጸሙ ስለመሆናቸው ምርት ከጀመሩበት ዓመት መጨረሻ ጀምሮ በገቡት ውል መሠረት በየዓመቱ የግዥና ሽያጭ ውልና ደረሰኝ ማረጋገጫ በየደረጃው ለሚገኝ የቢሮው መዋቅር የማቅረብ፤

(4) ባለሃብቶች በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ (Environmental Impact Aassessment) መሠረት ያመላከታቸውን የአካባቢ ተጽዕኖን ለመከላከል የሚያስችሉ ቴክኖሎጅዎችን ከፕሮጀክቱ ግንባታ ጎን ለጎን የመፈጸም፤

(5) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ስር በተዘረዘሩት መስፈርት መሠረት ተወዳድረው መሬት የተሰጣቸው ባለሃብቶች ማወዳደሪያ መስፈርትን ለማሟላታቸው በገቡት ውል መሠረት የመፈጸም፤

(6) ባለሃብቱ ባቀረበው ፕሮጀክት መሠረት ቦታ ከተረከበና የግንባታ ፈቃድ ከወሰደ በኋላ በጸደቀው የግንባታ ዲዛይን መሠረት ብቻ የመገንባት፤

(7) መሬት የተሰጠው ባለሀብት የግንባታ ፈቃድ ከማግኘቱ በፊት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ማረጋገጫ የማቅረብ፤

(8) የአገር ዉሥጥ ባለሃብትና በዉጭ አገር የሚኖሩ ትዉልደ-ኢትዮጵያዉያን ባለሃብቶች ፕሮጀክት አቅርበዉ ተገምግሞ ካለፈ በኋላ መሬት ለመዉሰድ አንድ ሳምንት ሲቀራቸዉ የጠቅላላ የኢንቨስትመንት ካፒታሉን 5 በመቶ በዝግ አካዉንት የማስያዝ.

(9) የመሥሪያ ቦታ/መሬት የወሰዱ ባለሀብቶች በገቡት ውል መሠረት ወደ አፈፃፀም ካልገቡ መሬቱ ተነጥቆ ወደ መሬት ባንክ እንደሚገባ የማወቅ፤

(10) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) መሠረት የመሥሪያ መሬቱ/ቦታው ለሌላ ባለሀብት እንዲተላለፍ ሲደረግ ቦታው የሚተላለፍለት ባለሀብት የመሬት ካሳውን ወቅታዊ ግምት ከፍሎ የሚወስድ ሲሆን፤ በግለሰብ የተከፈለ የመሬት ካሳ ከሆነ መሬቱ ተነጥቆ በሚተላለፍበት ጊዜ የሚተላለፍለት ባለሀብት ለተነጠቀው ባለሀብት የሚከፍለው የመሬት ካሳ የተነጠቀው ባለሀብት ቀደም ሲል የከፈለውን ካሳ ብቻ እንደሚሆን የማወቅ፡፡

(11) ለአምራች ኢንዱስትሪ የተሰጠን የመስሪያ ቦታ/መሬት ለግለሰብ በብድር ወይም በሌላ እዳ ማስያዝ አይቻልም፡፡

20. በዝግ አካውንት የተያዘን ገንዘብ ስለመልቀቅ፡-

(1) ለአቅም ማሳያ በዝግ አካውንት የተያዘ ገንዘብ የሚለቀቀው የፕሮጀክቱ የመሠረት ግንባታ (Foundation work) መጀመሩ በቢሮው መዋቅር ሲቭል መሃንዲስ እና በፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ባለበት በኮርፖሬሽን ባለሙያዎች ሲረጋገጥ ሙሉ በሙሉ የሚለቀቅ ይሆናል፤

(2) ባለሀብቶች የአቅም ማሳያ የባንክ ትራንዛክሽን ከአንድ የፋይናንስ ተቋም በላይ ማቅረብ የሚችሉ ሲሆን፤ ኢንድ ባላንስ በዝግ አካውንት የሚያቀርቡት ደግሞ ከአንድ የፋይናንስ ተቋም ብቻ ይሆናል፤

(3) ለአምራች ኢንዱስትሪ የተሰጠን መሬት ግንባታው ሙሉ በሙሉ ተጠናቅቆ ምርት ማምረት ከመጀመሩ በፊት መሸጥ፣ መለወጥ ወይም ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ አይቻልም፤

(4) በፒ.ኤል.ሲ. እና በሽርክና ማኅበር ስም ለአምራች ኢንዱስትሪ የተሰጠን መሬት ግንባታው ሙሉ በሙሉ ተጠናቅቆ ምርት ማምረት ከመጀመሩ በፊት ፕሮጀክቱ ሲገመገም በመመሥረቻ ጽሑፉ እና መተዳደሪያ ደንቡ ላይ ከነበሩት አባላት ውጭ በባለቤትነት ይዞ መገኘት አይቻልም፤

(5) የመዋቅሩ ባለሙያ ለግምገማ የሚቀርብን ፕሮጀክት በራሱ አዘጋጅቶ ከተገኘና ይህም በማስረጃ ሲረጋገጥ ሕጋዊ እርምጃ የሚወሰድ ይሆናል፤

(6) በዚህ መመሪያ መስተናገድ የማይችሉ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ካሉ በልዩ ሁኔታ በየደረጃው በሚገኘው የቢሮው መዋቅር አስተያየት እየተሰጠ በክልሉ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ በኩል የመጨረሻ ውሳኔ የሚያገኙ ይሆናል፡፡

ክፍል ስምንት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

21. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

(1) በቢሮው ወደ ሁለ-ገብ ኢንዱስትሪ ፓርክና ክላስተር ማዕከላት የሚገቡ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ምልመላና የመሬት መጠን ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 01/2013 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፤

(2) ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማናቸውም መመሪያ ወይም ሰርኩላር ወይም ልማዳዊ አሠራር ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

22. መመሪያውን ስለማስፈፀም

(1) በየደረጃው የሚገኝ የቢሮው መዋቅር እና ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ባሉበት ከተሞች ኮርፖሬሽኑ ይህን መመሪያ ተፈጻሚ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

(2) ይህን መመሪያ በመተግበር ሂደት አንድን ሰው አላግባብ ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት በማሰብ አላግባብ የተረጎመ በየደረጃው የሚገኝ የቢሮው ባለሙያ ወይም ኀላፊ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

23. መመሪያውን ስለማሻሻል

አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ቢሮው ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

24. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ የቢሮው ኃላፊ ከፈረመበት ከቀን -------------2015 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡